# <u>ማዕቀብ ትግል ነው፤ ማዕቀብ ፍቱን ነው!</u>

**አምሀ ደሳለኝ ዘቁስቋም**

መጠቅን አወቅን የሚሉ ግለሰቦች የመለስ ዜናዊን ምርጫ በማዕቀብ መሸኘት ትክክል አይደለም ብለው መከራከር ጀምረዋል። የመለስ ደጋፊ ያልሆኑትም ማለት ነው።።። የሚሰጡት ምክንያት የተለያየ ነው--ሁሉም ግን የተሳሳተና አንዳንዴም የወጣለትን አድርባይነትን በጭምብ ልና በሽፋን የሚያቀረብ ነው።

ለምሳሌ የላባደሩ/የሰራተኛው ሕዝብ ዋና የትግል መሳሪያው የስራ ማቆም አድማ ነው። ይህን መብት ማለትም የስራ ማቆምን መብት የሚያግዱ አገዛዞች በመሰረቱ ፀረ ላባደር ናቸው። ሕዝብም በአጠቃላይ መብቱን ለማስከበርና ህገ ወጥ ድርጊቶችን ለመቃወም መነሳሳትና በአድማ ም ሆነ በሌሎች ስልቶች መጠቀም እንዳለበት የሚታወቅ ነው። ማዕቀብ አንድ ወሳኝ የሕዝብ የትግል መሳሪያ ነው። በወያኔ ምርጫ መግባት ፋይዳ ቢስ ለመሆኑ በ1997ቱ የተከሰተው አሰቃ ቂ ሁኔታ በቂ ምስክር ነው። ከዚያ እስከዛሬ የተለወጠ አንድም መጥፎ ሁኔታና ጠባይ የለም። ተባብሷል። መለስ ዜናዊ የምርጫ ህጉን ለራሱ አሳምሮ አፀድቋል። የምርጫው ኮሚሽንም ባለፈ ው እንደታየው ሁሉ የወያኔ መሳሪያ ነው። ከወያኔ ጋር በቅርቡ ሰነድ የተፈራረሙት ራሳቸው ሳይቀሩ እንዳመኑት የወያኔ ቡድን ህግን አያከብርም፤ አሁንም ተቃዋሚዎችን ያንገላታል፤ ያስራል፤ ለረሀብ የመጣውን የምግብ እርዳታ ሳይቀር ለዚሁ የፖለቲካ ግቡ እየተጠቀመበት ነው። በየእስር ቤቱ የታገቱት የፖለቲካ እስረኞች አልተፈቱም፤ በቅርቡ የተያዙትም እየተደበደቡ ለመሆናቸው አንድ ዓይናቸው በድብደባ ጠፋ የተባሉት ጄኔራል አሳምነው ፅጌ ምስክር ናቸው። የመለሰቡድን አስገድዶና ገዝቶ ወደ 5 ሚሊዮን በላይ የኢሕአዴግ አባል መልምሏል። ታዛቢዎች ም እኔ የምፈልጋቸውና የምፈቅድላቸው ብቻ ይሆናሉ ሲል መለስ ራሱ ተናግሯል። ፖሊሱ፤ ፀጥታው፤ ምርጫ ቦርዱ፤ ቆጣሪው፤ ሳጥን ከፋች ዘጊው ሁሉ በወያኔ ቁጥጥር ስር ያለ ነው። ስለዚህም ይህ ሁሉ ፍትህን ከልካይ ሁኔታ ባልተቀየረበት በወያኔ ምርጫ ዘው ብሎ መግባት ከሞኝነት በላይ ነው።

በዚህ ሁኔታ ሕዝብ ያለው አማራጭ መቸስ ምን ይደረጋል ብሎ ለወያኔ መሳሪያ መሆን ሳይሆን ማዕቀብ ማድረግ ነው። ባለፈው የማሟያ ምርጫ ጊዜ እንዳደረገው። ማዕቀብ ተቃውሞ ነው። ማዕቀብ ትግል ነው። እጅ አለመስጠት ነው። ተቃውሞን በዓለም አቀፍ ደረጃ ማስተጋባት ነው። ይህን የሚቃወሙ አንዳንዶች መድረኩን ወይንም ምርጫውን ለወያኔ መተው የለብንም ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ቀሰ በቀስ ሀይላችን ይጠናከራልና በምርጫው መግባት አለብን ይላሉ። ትጥቅ ትግል የተባለው የት አለ? በሚል ጥያቄም ይነሱና ታዲያስ ምን ይደረግ በምርጫ እንግባ እንጂ ወደሚል መደምድሚያ በአፋጣኝ ይደርሳሉ። የአድር ባይነት ትንተና የባጡን የቆጡን ጠቃቅሶ ያው የሚጠበቀው መደምድሚያ መድረስ መሆኑ ይታወቃል። ወያኔ ድሮውንስ በምርጫ ተገባ

አልተገባ መች ስልጣን ሊያቀምስ? መች የሕዝብን ድምፅ ሊያከብር? መጠየቅ ያለበት መሰረታዊ ጥያቄ ግን በኢትዮጵያ የነፃና ፍትሀዊ ምርጫ መድረክና ዕድል አለ ወይ የሚለው ነው:: በሩ ገርበብ ብሏል ይሉ የነበሩት ፕሮፌሰር ራሳቸው ዛሬ በሩ እንደ ቃሊቲ በር ክርችም ብሎ መዘጋቱን ማመን ተገደዋል:: የነፃ ምርጫ ጭላንጭልም የለም:: በ1997 የነበረው ሁኔታ ራሱ ዛሬ ጭራሹኑ የለም:: ወያኔ በወያኔነቱ ጎምዝዟል፤ ከፍቷል:: በእርግጥ ተወዳዳሪ ነን ለሚሉት ፈጣሪን ከፈራ ወይም የጡት አባቶቹን ምክር ከሰማ ጥቂት ወንበሮች ወይም መባል እንደጀመረው በርጩማዎች ይለቅ ይሆናል (ባለፈው ማሟያ ምርጫ ግን አላቀመሰም) :: የተወሰኑ እስረኞችንም ፈቶ ፍትህ ሰፈነ ብሎ ጥሩምባ/ ሊነፋም መቻሉ መጠበቅ ያለበት ነው:: ይህ ሁሉ ግን ቢከፍቱት ተልባ ቢዘጉት ጉም ነው:: መሰረታዊ ለውጥን አያሳይም፤አያመጣም:: ሌላ በምርጫ ለመሳተፍና ማዕቀብን ለመቃወም የሚቀርበው ምክንያት በምርጫ ካልተሳተፍን እንታገዳለን የሚል ነው:: ለነገሩማ ህጋዊ ተቃዋሚ ማለት ተቃዋሚ እንጂ ተለጣፊና የገዢው ድርጅት ሎሌ መሆን ማለት አልነበረም:: ሁለተኛ ደግሞ ፀረ ሕዝብን አገዛዝ ስንታገል መታገድ ሳይሆን መገደልም ያለ መሆኑ ቢያንስ ከ 1997 ጀምሮ መታወቅ ያለበት ነው:: ታዲያ እገዳ ቢመጣ ይህ ከባድ ዋጋ ሆኖ ነው? ለሕዝብ የቆመ ድርጅት በወያኔ ኢፍትህዊ ምርጫ አልገባም ብሎ መቆም ይጠበቅበታል:: ያስከብረዋልም ይህ አቅዋሙ::መግባቱ ነው ስህተት የሚሆነው::

ለዚህም ነው ይህን ሀቅ የሚቀበሉ ክፍሎች ማዕቀብን የሚጠሩትና ጥሪያቸውም ወቅታዊና ትክክ ል የሚሆነው:: ወያኔ በራሱ የራሱን ሳጥን ሞልቶ እንዳለፈው ማሟያ ምርጫ መሳለቂያ ሆኖ ይጋለጥ:: በግንቦት 2002 የወያኔ ምርጫ ሕዝብ መሳተፍ የለበትም:: ማዕቀብ ነው የትግሉ መሳሪ ያና መንገድ:: ማዕቀብ ያለውንና ሊኖረው የሚችለውን አንደምታና ጥቅም መረዳት የተሳናቸው ሁሉ በጊዜ ለማወቅና ለመማር መጣር አለባቸው:: የስራ ማቆም አድማ፤ የሙት ከተማ አድማ፤ ማዕቀብ ወዘተ የሕዝብ የትግል መሳሪያዎች ናቸው:: በተለይም ሰላማዊ ትግል የሚሉ ክፍሎች ይህንን መረዳትና ማስተጋባትም ነበረባቸው:: ሰላማዊ ትግል ሁሌም ለገዢው ድርጅትና ሀይል ጎንበስ ማለትና በከንፈር መጠጣ መንጎድ መጠረዝ አለመሆኑንም ማወቅ ያስፈልጋል:: በወያኔና ቅጥረኞቹ ላይ ሁለገብ ማዕቀብ ይደረግ ተብሎ የነበረው ትክክል ነበር፤አሁንም ነው:: ለዚህም ነው ከልብ ለሕዝብ የቆሙ ድርጅቶች ከወያኔ ምርጫ ራሳቸውን ማግለል ያለባቸው::ለዚህም ነው ሕዝቡ በሞላ በተቻለው መጠን ማዕቀብ ያደርግ ዘንድ መቀስቀስና መደራጀትም ያለበት:: በዋዛ ፈዛዛ ልብ መግዛትና ከሕዝብ ተመክሮ ትምህርት መገብየት አቅቶን ወያኔ ከዛሬ ነግ ወያኔነቱ ይቀረፋል፤ ይለወጣል በሚል አጉል ተስፋ የምንባዝን ከሆንን ቀንበራችንን ተሸክመን መቃብር እንገባለን:: ከዚህ እስከ ግንቦት ወያኔ የሚያስመዘግበው ለውጥ ሊኖር አይችልምና እንጠብቅ ብሎ ክርክርም ትጥቅ አስፈቺና ለወያኔም የሚጠቅም ነው::ከዛሬው ጀምሮ አቅዋማችን የግንቦቱ ምርጫ ውጤት ዛሬ ይታወቃልና በሂደቱ አትግቡ፤ማዕቀብ አድርጉ የሚል መሆን አለበት:: ሌላ ው ሌላው ጨዋታ ቀስ በቀስ በእግሩ ይሄዳል የተባለው ዕንቁላል መበስበሱን አለመገንዘብ ነው::